# ዳሰሳ

## ወሬኛን ትም!

ካሣ ዘለቀ፣ በጡረታ ላይ የሚገኙ የቀድሞ የሕ/ግ ባለሙያ

« ጦር ከፈታው ወሬ የፈታው » የሚለው ይትበሃል ከአበው ሲወርድ ሲወራረድ የመጣ መሆኑ ብቻ ሳይሆን የአንድ ዘመን ብቻ ተረት ሆኖም አልቀረም ። ይባስ ብሎ በአፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ማኅበረሰቡ በወሬ እንዴት ይታመስ እንደነበር ምክር አዘል ስንኝ አስቋጭቷል።

« በአዲስ አበባ ወሬ በ'ንጦጦ ንፋስ ፣ እያያችሁ አውሩ ምንተ ክርስቶስ። »

በዚያን ዘመን በአዲስ አበባ ወሬ ምን ያህል ፈጣን እንደነበረና ችግር ፈጣሪነቱ ስለጐላ ፣ ግራ ቢያጋባቸው የዚያን ዘመን ሰዎች ክርስቶስ አንድ እንዲል ተማጽነዋል።

በዚያን ዘመን አፄ ምኒልክ ከሹማምንቱ ጋር በምሥጢር ስብሰባ አካሂደው የሚወስኑት ውሳኔ አዋጅ ሆኖ ከመውጣቱ በፊት ከሕዝብ ጆሮ ደርሶ በየመጠጥ ቤቱና በየአደባባዩ የመወያያ ጉዳይ እየሆነ ስላስቸገራቸው አንድ ዘዴ ስለመዘየዳቸው የሚነገርላቸው አፈ ታሪክ አለ። አፄው አንዱን ባላገር ያስጠሩትና ቤተ መንግሥት ይገባል። እንደደረሰም እጅ ነስቶ ከፊታቸው በድንጋጤ ይቆማል ።

« አይዞህ አትፍራ ፤ ያስጠራንህ ለቁም ነገር ነው፤ ምሥጢር ደባቂ እንደሆንክ ይነገራል፤ እውነት ነው?»

ይሉታል። « ይሆናላ ጌታዬ ፤እኔ ምናባቴን አውቄ?» ይልና አንገቱን ያቀረቅራል።

«የምልህን ከልብ አዳምጥና በምሥጢር ያዘው! »

« እሺ ጌታዬ ምን ገዶኝ። »

« ሰሞኑን ቀንድ አወጣለሁ ፤ይህችን ምሥጢር ከሌላ ሰው ጆሮ ደርሶ ብሰማ ወዮልህ! በል በመጣህበት እግርህ ተመለስ። » ብለው ያሰናብቱታል።

ምሥጢሩ የተነገረው ሰው ራሱ ሊፈነዳ ደረሰ። ለሚስቱ ሊናገር ከጀለ ፤ "ለጐረቤት ብታወራስ?" አለና ቻለው። ለጓደኛው ለመንገር ፈለገ ፤ ፍርሃት ዋጠውና ዝም አለ። ለማን ነግሮ ትንሽ ተንፈስ ሊል እንደሚሻለሁ ቢያወጣ ቢያወርድ በሁሉም ሰው ላይ እምነት አጣ።

ለብዙ ቀናት ከራሱ ጋር ሲጣላ ከቆየ በኋላ አንድ መላ መጣለት፤ ውስጣዊ ስሜቱም ተቀበለው፤ መንገድ ጀመረ ፤ከሠፈሩ ብዙም እርቆ አልሄደም። ዙሪያ ገባውን ቃኘ –እንኳን ሰው ወፍም ዝር አይል። ገልመጥ ፣ ገልመጥ አደረገና እንደመጐንበስ ብሎ የመሬቱን አፈር በጣቶቹ ጫር ጫር አደረገ። አፉን ወደቆፈረው ጉድጓድ ተክሎ « ንጉሡ ሰሞኑን ቀንድ ያወጣሉ!» አለና በረጅሙ ተነፈሰ። የማሳትን ጉድጓድ አፈር መለስ አደረገና በቀኝ እጁ መዳፍ ተምትሞ ወደቤቱ ተመለሰ። ቀለል አለው። ከጥቂት ጊዜ በኋላ እንዳጋጣሚ ከአፈሩ ጋር አብራ የገባች የቅል ፍሬ በቅላ አድጋ አፈራች። አካባቢው ያሉ ነዋሪዎች የበሰለውን ቅል ቆርጠው ወደ ገበያ ወሰዱት። አንዳንዱ ለጥጥ መንደፊያ ዋለ። የደጋኑን ቀጭን ጅማት ሲያነዝሩበት የሚያሰማው ድምፅ «ንጉሡ ቀንድ ሊያወጡ ነው፤ አፄ ቀንድ አወጡ!» ሲል ተሰማ።

ለሌሎችም አገልግሎት የሚሰጡ የዚሁ ቅል ውጤቶች ተመሳሳይ ድምፅ ያሰሙ ጀመር፡፡ የሰማው ሁሉ በሁኔታው ሲገረምና ሲደነቅ ወሬው በከተማዋ ሁሉ ናኘ ፡፡ እምብዛም ሳይቆይ አፄ ምኒልክ ጆሮ ደረሰ ፡፡ የሰሙትን ሁሉ የቅርብ ባለሙዋሎቻቸው ሁሉ አጫወቷቸው፡፡ በተለይ «ንጉሡ ቀንድ አወጡ!»የሚለው የቅሎች ድምጽ በርካታ መሆኑ ተነገራቸው፡፡

በሁኔታው በጣም በመገረም ምሥጢር እንዲደብቅ የተነገረውን ባላገር አስጠሩት፡፡ እሱም እየተርበተበተ ቀርቦ ከፊታቸው ቆመ፡፡

«እንዴት ታማኝ ነህ ብለን የነገርንህን ለሌላ አሳልፈህ አወራህ? » አሉት፡፡ «ጌታዬ ለማንም አላወራሁም ሚስቴን እንኳን አላመንኳትም፡፡ ግን ለራሴ ብቻ መያዝ ስላስጨነቀኝና የማወራው ስፈልግ ሁሉንም ሰው ባለማመኔ መሬቱን ጫር ጫር አድርጌ 'ንጉሡ ቀንድ ሊያወጡ ነው' ብዬ አፈሩን መለስኩት፡፡ እንግዲህ እንኳን ሰው መሬቱም አይታመንም ማለት ነው፡፡ አጥፍቻለሁ ንጉሥ ይማሩኝ» ብሎ ከንጉሡ ምሕረት እንደተደረገለትና በሰላም ወደ ቤቱ እንደተመለሰ አፋዊ ታሪክ ሆኖ አሁን ድረስ እየተነገረ ይገኛል፡፡

***

ጨዋታን ጨዋታ ያነሳዋል ፡፡ በ1960ዎቹ የሰማሁትንና ያየሁትን የወሬ ወረርሽኝ ላጫውታችሁ፡፡ ቦታው ዮሴፍ መካነ መቃብር ነበር፡፡ በከተማው አስደንጋጭና አጓጊ ወሬ ተናፈሰ፡፡ ይኸውም «መቃብር ውስጥ ያለው ሙት ልክ በአሥር ሰዓት ሦስት ጊዜ እያቃጨለ ድምጽ ያሰማል ፤ቀጥሎ ስለዓለም ፍፃሜ ይሰብካል» የሚል ነበር፡፡

የአዲስ አበባ ወሬኛ እንኳን ይህቺን አግኝቶ እንዲያውም እንዲያው ነውና እንደ ጉድ ባገኘው ትራንስፖርት ወደ ዮሴፍ ነጐደ፡፡ እኔም ከሌሊቱ አሥር ሰዓት በፊት ደረስኩ ፤ ነፍሱን ይማረውና ጋዜጠኛ ጳውሎስ ኞኞም በቦታው ተገኝቶ ከፊት ለፊት ቆሞ አየሁት፡፡ አንድ ዲያቆን መጣና ከመቃብር አጠገብ ቆመ፡፡ ለተሰበሰበው ሕዝብም እንዲህ ሲል ተናገረ፡፡

«ልክ አሥር ሰዓት ሲሆን የቃጭል ድምፅ ይሰማል፤ ሦስት ጊዜ ነው ፤ ከዚያ ስለምፅዓት ይናገራል ፤ ክርስቶስ ምን ይሳነዋል፡፡» እያለ ደጋግሞ ገለፃ አደረገ፡፡ የተጠበቀው አሥር ሰዓት እየተቃረበ መጣ፡፡ ሁሉም ዐይኖቹን ሰዓቱ ላይ ደጋግሞ ተከለ፡፡ ድንገት የቃጭል ድምጽ ተሰማ፡፡ ለወሬ ያሰፈሰው ሕዝብ ወደኋላው ሲሸሽ አንዱ ባንዱ ላይ እየተነባበረ ትልቅ ጉዳት ደረሰ፡፡

ጳውሎስ ኞኞ እንደተጋደመ ዐይኖቹን መቃብሩ ላይ አሳረፈ፡፡ ለሚች ፎቶ ሽፋን የተዘጋጀችው መስታወት ነፋስ በነካት ቁጥር ማቃጨሏን ቀጥላለች ጳውሎስ በደረቱ ተስቦ በጣቱ ጫን አላት ፤ ፀጥ አለች፡፡ ለቀቃት– ነፋስ ሲነካት ደግማ አቃጨለች ፤ የሚሰማ የሙት ንግግር ግን ፈጽሞ አልነበረም፡፡

ወደ ኋላ አፈግፍጐ ከሩቅ በፍርሃት ይመለከት የነበረውን የወሬ ሠራዊት ጠርቶ ሁኔታውን አስረዳ ፡፡ በተግባርም አሳያቸው፡፡ በነፋስ ምክንያት ድምጽ የምታሰማው መስታወት የሞተውን ሰው ነፍስ አዘርታ ለማናገር አበቃች፤ብዙ የተባለለት የምፅዓት ስብከትና ማስጠንቀቂያ በሬ ወለደ ወሬ መሆኑ ተረጋገጠ ሁሉም በመጣበት እግሩ በሞኝነቱ ስቆ ወደየመጣበት ተመለሰ፡፡

ምን ይሄ ብቻ፡፡ በዚያው ዘመን ደግሞ እንዲህ ሆነላችሁ፡፡ « ራስ መኮንን ድልድይ ወንዙ አለት ላይ የተቆራረጠ የሰው እጅ በጋዜጣ ተጠቅልሎ ተጥሏል» የሚል ወሬ ተናፈሰ፡፡ የወሬ እፍታው ከጠዋቱ የደረሰው የፒያሳና አራት ኪሎ ሰው እንዲሁም የወሬ ሱስ የጠናበት መንገደኛ ሁሉ የድልድዩን ጠርዝ አስጨንቆታል፡፡ የአባ ዲና ፖሊሶች እስኪመጡ ወደ ወንዙ ሕዝቡ እንዳይወርድ ፖሊሶች በመከላከል ላይ ናቸው ፡፡ ጋዜጠኞች መጡ፡፡ ግና ከመድረሳቸው ራሳቸውን ይዘው

«አቤት! እምኑ ዘመን ላይ ደረስን? ከጠዋት ጀምሬ የዚህን ጭካኔ ጉድ ለማየት ቆሚያለሁ » እያሉ ሲብከነከኑ ከነበሩ ሰዎች መካከል አንዱ ጠጋ ብሎ ፣ «እማማ ወርደው አይተው ነበር?»አላቸው፡፡

«እንዲህ ዓይነቱ ጭካኔ እንዴት ይታያል ፤ ፖሊሶች ሳይመጡ ወርደው አይተው የመጡ ነገሩኝ፡፡ አቤት ጭካኔ...» «ምን አሉዎት?» «የጥፍሯ ቀለም እንኳን አልደረቀም !» አሉኝ ልጄ፡፡ አይ ዘመን? ሁሉም በየፊናው እንዳሮጊቷ የሰማውን ወሬ ሲያብጠለጥል የአባዲና ፖሊሶች ከተፍ አሉ፡፡ ለወሬ ባሰፈሰፈው ሕዝብ መካከል ሰንጥቀው ወረዱና በጋዜጣ ከተጠቀለለው ነገር «የእጅ ቁርጥራጩ» ሁኔታ ለማየት ጥቅሉን በጥንቃቄ በመቀስ ተርተር አደረጉት፡፡ በእጅ ቁርጥራጭ ፈንታ የተገኘው የጫት ገረባ ሆኖ አረፈው፡፡ አባዲናዎቹ የአዲስ አበባ ወሬኞች በፈጠሩት ያልተረጋገጠ ወሬ ምክንያት በከንቱ መድከማቸውን እየተራገሙ ራሳቸውን በአግራሞት በማወዛወዝ ወደመጡበት ተመለሱ፡፡ ለወሬ ያሰፈሰፈውም ሕዝብ ተበተነ፡፡ «ጉድና ጅራት ወደኋላ ነው» በዚህ ዘመን ደግሞ ሌላ ወሬ ተሰማ የአዲስ አበባ ሕዝብ ዳር እስከዳር ተነቃነቀ፡፡ ነገሩ እንዲህ ነው፡፡

«አሮጌው አውሮኘላን ማረፊያ ጦር ኃይሎች አካባቢ አንድ ወንድና ሴት ከትዳራቸው ውጪ ሲማግጡ ቅዱስ ገብርኤል በዕለተ

ቀኑ አጣበቃቸው፤ ለማለያየት ቢፈለግ አልተቻለም ፤ሕዝብ ይህን ገድል እንዲያይ ስለተፈቀደ በአውቶቢስና በቤት መኪና በታክሲ እየጐረፈ ነው። » ተብሎ ወሬው አዲስ አበባን አናወጣት። ሕዝብ ለወሬ ሲል በነቂስ ወጣ። ቦታው ሲደረስ ትርምስ ብቻ እንጂ ምንም ፍንጭ ጠፋ ። ውሸት መሆኑን በአካባቢው ያሉ ሰዎችና የሚመለከታቸው ወገኖች ሁሉ አስተባበሉ ፤ ፀሐይ ሲቀቅለው የዋለውና ለወሬ ሲል ለወጪ የተዳረገው ሁሉ በመጣበት እግሩ ተመለሰ።

አብዛኛው ወሬኛ እንኳን በቁም ያለውን ይቅርና እስከወዲያኛው ያሸለቡትን እንኳን ከሞቱበት እያስታወሰ እገሌ፣ እገሊት … በማለት ያለ የሌለ ዘግናኝ የሆነ የታሪክ ጉድፍ ሲለቀልቅባቸው ይሰማል። መቼስ ምን ይደረግ? ሙታን ቀና ብለው አያስተባብሉ። አንዴውኑ አርፋዋልና በስማቸው ምን እየተሠራ ወይ እየተባለ እንደሆነ አያውቁ። – ወሬኞች ግን ሙታንን የሠፈር ቡና ማጣጫ፣ የመሸታ ቤት ጨዋታ ማድመቂያ፣ መሳቂያና መሳለቂያ ሲያደርጓቸው ትንሽም እንኳን ለአፋቸው ለከት አያበጁለትም። ምን ያድርጉ የወሬ ሱሰኞች ናቸው። ሱስ ደግሞ በቀላሉ የሚገላገሉት ባሕርይ አይደለም። «ሥራ ፈት አዕምሮ የተንኮል መጠንሰሻ ነው።» እንደሚባለው ሁሉ ትክክለኛውንና ጤናማ ኀሊና የተላበሰውን እኛነታችንን በማሳወቅ ቦታ ስብዕናችንን ወደሚያናጋ ተጨባጭነት ለሌለው የሀሰት ወሬ ጊዜያችንን እያቃጠልን ዕድሜያችንን በመግፋት ላይ የምንገኝ ወገኖች በቶሎ ሳይመሽ ወደየኀሊናችን እንመለስ። ለማንኛውም ይህቺን ጽሑፍ እንዝለቃት።

«ወሬኛን አፉን ትም!»

«ጦር ከፈታው ወሬ የፈታው»

« ለወሬ ሞትኩ»

« የወሬ እናት»

« በወሬ ያቃመሱት »… ስለ ወሬና ወሬኛነት ብዙ ብዙ ተብሏል። ለበርካታ ዓመታት ለዕድገታችን ማነቆ ሆኖ የኖረውን አጓጉል ባህል ለመግታት ያልቻለው ምሁር ተብዬ እንኳን በትላልቅ የትምህርት ተቋማት ያልሆነና ፍፁም ሊታመን የማይችል የፈጠራ ወሬ ሲሰማ ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ ትንሽ እንኳን ፍላጐት ማሳየት ይቅርና ራሱም ገብቶ በወሬ ዝንኮራው ሲተራመስና ሲታመስ ይታያል ።

የአንድ በቅርብ የማውቀው ወዳጄ የዱሮ አለቃ ዕኩይ ድርጊት ሁልጊዜ ይታወሰኛል። ነፍሳቸውን ይማረው እንዳልል ከሚከተሉት ሃይማኖት በተቃራኒው አዘውትረው ይጓዙ ስለነበር ምሕረት ያገኛሉ የሚል እምነት የለኝምና ይቅርብኝ።

አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ያለችሎታቸው በዚህም በዚያም ብለው ኃላፊነት ቦታ ላይ የመቆናጠጥ ዕድል ያገኛሉ። ዕውቀቱም ሆነ በራስ መተማመኑ ስለሚጐድላቸው ውስጣቸውም ባዶ ስለሆነ ዘወትር ጆሯቸውን ለወሬ ከፍተው ይሰጣሉ። ስሜታቸውን የተገነዘቡ ምንዝሮቻቸውም ደግሞ ከምናባቸው እየፈጠሩና በቃላት ጨዋታ እያጣፈጡ ደህና አድርገው ስለሚግቷቸው የጥቃት ሰይፋቸውን ከአፎቱ አውጥተው ለብቀላ ቀንዳቸውን ማቆም ይጀምራሉ። ታዲያ ከፍ ሲል የጠቀስኳቸው የቀድሞ ወዳጄ የቅርብ አለቃ ሲፈጥራቸው ቅንጣት ታህል የአስተዳደርም ሆነ የፋይናንስ ደንብ ዕውቀት ባጠገባቸው አላለፈም ነበርና ከቀን ወደ ቀን ሥራቸውን እንደ ዛፍ እየገዘገዙ ከፊት ለፊት በከንቱ ውዳሴ የሚያሞግሷቸውን ደካሞች በየደቂቃው እያስተናገዱ ሥራውን መበደል ይቀጥላሉ። ከሥራቸው ያለው ምክትል ደግሞ ታዋቂ የሆነውንና ሊዘጋ ተቃርቦ የነበረውን ድርጅት እንዲያድን ለበርካታ ጊዜያት እግሩ ላይ መውደቅ እስኪቀራቸው ድረስ ለተደጋጋሚ ጊዜ ለምነው ሥራውን ካስጀመሩት በኋላ ከበሳል የድርጅቱ ባልደረቦች ጋር ነባር ችግሮችን በግሩም ሁኔታ አስተካክሎ መሥራት ይጀምራል።

ለሠራውም አኩሪ ተግባር በሥራ ባልደረቦቹና በተገልጋይ ድርጅቱ ደንበኞች አድናቆትን ይቸራል። በሥሩ ያሉ አስመሳዮችና መዝባሪዎች እንደፈለጉት መሆን ባለመቻላቸው ዋናውን የድርጅቱን የሥራ መሪ በወሬና አሉቧልታ በመዳፋቸው ሥር አስገብተው እንደራስ ሆቴል በር ወደ ፈለጉበት አቅጣጫ እያሽከረከሩ ምክትላቸውን እንደ ወገብ ቅማል ጠምደው ይይዙታል። ወሬኞቹ የውስጥም ሆነ የውጭ ኦዲተር ከማያውቀው ካዝና ብር እየተዘገነ እየተሰጣቸው መንበሽበሹ ይዘወተራል። በሰመረላቸው አጋጣሚ ሁሉ ድርጅቱን ከመሰል መዝባሪዎች ጋር በመመሣጠር ሲመገምጉት ይታያሉ። ለአብነት ያህል ከላይ የተጠቀሰውን ድርጅት ንቅዘት ጠቆም አደረኩ እንጂ እስቲ በሌሎች ተመሳሳይ አገልግሎት ሰጪና የንግድ ተቋሟት ሁሉ እውን ጆሮውን ለአሉቧልታና ለፈጠራ ወሬ ሳይሰጥ በተሠማራበት ሙያ ጥራትና ብቃት ያለው የሥራ ክንውን የሚያሳየው ምን ያህሉ ነው? ሌላው ደግሞ የትም የትም ይሁን እስቲ በተቃራኒ ጾታዎች ላይ ያለውን የወሬ ናዳ ደግሞ እንዳስስ። የሥራ ባልደረባዬና የቅርብ ጓደኛዬ ነው። ብዙ ጊዜ መድሐፍ ከእጁ አይለይም ፤ ለዚህም ነው መሰል በነገሮች ላይ ያለው አመለካከት በጣም በሳል ነው። ለሚያየው ሆነ ለሚናገረው ሁሉ ጠለቅ ብሎ መመራመርና ሃቁ ላይ መድረስ ይወዳል ፤

ለሚያማክሩት ሁሉ ለችግሮቻቸው ቀና መንገድ ይከፍትላቸዋል ፤ በዚህም የተነሳ ብዙዎች ይቀርቡታል ፤ ምሥጢር ጠባቂ ነው፤ ለሚጠጉት ተቃራኒ ፆታዎች ከፍተኛ ክብር ይሰጣል ፤ ይወያያል ፤ የመፍትሔ ሀሳብም ይሰጣል፡፡ በዚህ ቁም ነገረኝነቱም ይመስላል አንዲት የሥራ ባልደረባችን ከእሱ ጋር በግቢ አዘወትራ ትታያለች፡፡ ባለትዳርና፣ ከቆንጆ ቁመና ጋር መልከ ቀና ናት፤ የምትታወቀውም በኮስታራነቷ ነው፡፡ ነገር ግን ከዚሁ ጓደኛዬ ጋር በግቢ ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ቁመውም ሆነ ተቀምጠው አፍ ለአፍ ገጥመው ሲያወሩ ይታያሉ ፤ ወሬኛ ሁሉ ግራ ገባው፡፡ በሀሜትም ያብጠለጥላቸው ጀመር ፤ ጭራሽ ይባስ ብለው «በዛብህና ሰብለወንጌል» የሚል ቅጽል ስም አወጡላቸው፡፡

በርካታ ወሬኞች ሥራዬ ብለው በግንባርና በስልክ «ጓደኛህን ለምን አትመክረውም? የልጆች እናት መሆኗን እያወቀ ለምን ትዳሯን ሊበትን እንደዚህ ባደባባይ… አላበዛውም ? … በኋላ ባሏ አንድ ነገር ቢያደርገው እኮ ፀፀቱ ላንተም ነው! … ተው በለው፡፡» ሲሉኝ ፈገግ እያልኩ « እንዴት እስከዛሬ አብራችሁ እየኖራችሁ የእሱን ባሕርይ አታውቁም ? እውን እንደምትሉት ዓይነት ሰው ነው?» ስላቸው «ሰው እኮ ነው ሊለወጥ ይችላል ፤ ደግሞም ልጅቱ እንዴት እንደምታምር አንተም ሳታውቅ ቀርተህ አይደለም፡፡ እንኳን እሱን መነኩሴ ከገዳም ታስኮበልላለች! ታዲያ እሱ አይሸነፍም ብትል በዚህ ግቢ ውስጥ ማን ያምንሃል? … ይልቅስ ምከረው እንቢ ካለ መከራ ይመክረዋል!› የሚሉና ተመሳሳይ ሃሳባቸውን በተለያየ መንገድ የገለጹልኝ በርካታ ሰዎች ስለነበሩና «ውሸት ሲበዛ እውነት ይመስላል» እንዲሉ ሁኔታው ስላሳሰበኝ እሱንም እሷንም የስም ማጥፋት ዘመቻ እንደሰደድ እሳት እየተቀጣጠለባቸው መሄዱንና በርካቶችም እንዳናገሩኝ ነገርኳቸው፡፡

የጓደኛዬን ባሕርይ በሚገባ ስለማውቀው በበኩሌ ቅንጣት ታህል ጥርጣሬ አልነበረኝም፡፡ ለጥያቄዬ የመለሰልኝ «የሚባልግ ሰው ለዚያውም ባለትዳር እንዲህ ባደባባይ እንዴት ሊሆን ይችላል?» ሲለኝ እሷም ቀበል አድርጋ «ለመሆኑ በየትኛው መናፈሻ፣ ሆቴል አይተውን ነው? እንዲህ በሰው ሕይወት ገብተው መከራቸውን የሚያዩ? መንጋ ሥራ ፈት ሁላ! ከባለቤቴ ጋር አስተዋውቄዋለሁ ፤ ጓደኛሞች ናቸው፡፡ እኛን ለመጠየቅ መጥታ የነበረችውን እህቴን አይቷት ስለነበር ለጋብቻ የፈለጋት መሆኑን ለባለቤቴ ገልጾለት በጉዳዩ ላይ እየተወያዩ መሆናቸውን ጓደኛህ አላጫወተህም?» ስትለኝ ፣ የጀመረውን ከግብ ሳያደርስ ምንም ይሁን ምን ትንፍሽ እንደማይል ስለማውቅ አልደነቀኝም ፤ የገረመኝ ቢኖር የሠርጉ ዕለት ወሬኛው ሁሉ ምን ያህል እንደሚሸማቀቅ ነበር፡፡ ያም ሆነ ይህ በወሬ የተነሳ ለአብነት ያህል ለተቃራኒ ፆታዎች ያነሳሁት ቢሆንም ጓደኛዬ በወሬና በሀሜት ያብጠለጠሏትን ባለትዳር እህት አግብቶ የሁለት ልጆች አባት መሆን ብቻ ሳይሆን የሞቀና የደመቀ ትዳር ይዞ ይገኛል፡፡

ከላይ እንደጠቀስኩት በተለያዩ መ/ቤቶችና ድርጅቶች፣ ፋብሪካዎች ፣ ኢንዱስትሪዎች … ወዘተ ተቃራኒ ፆታዎች ቁመውም ሆነ ተቀምጠው እንዲሁም ሲሠሩ በወሬኞች ጭንቅላት ወዲያውኑ የሚፈጠረው የይሆናልና የጥርጣሬ የወሲብ ባህሪይ እንጂ ለቁም ነገር ነው ብለው የሚያስቡ ቢኖሩ በጣት የሚቆጠሩ ናቸው፡፡

በሠለጠነው ዓለም የትም ይሁን የትም እንኳን ተጨባጭ ባልሆነ ወሬ ተነስቶ በሰው ላይ ይቅርና ባመኑበት ማንኛውም ዓይነት ሕይወት ላይ ቢገዙ ዘወር ብሎ የሚያያቸው የለም፡፡ ከእነሱ ደግ ደጉን እየቀሰምን ለሀገር እድገት የሚውል ሥራ ወይም ዕውቀት ላይ ብንሰማራ አላስፈላጊ ፀብ፣ጭቅጭቅና ውዝግብ እንዲሁም መልካም ወዳጆቻችንንም ከማጣት እንታቀባለን፡፡ ትርፍ ጊዜ ካለን የወሬ ባህላችንን ወደ ንባብ ባህል መተካት አለብን፡፡

በመጨረሻ ለሥራ ፈት ወሬኞችና አሉቧልተኞች ጆሯችሁን የምትሰጡ ምሁራን፣ኃላፊዎች፣ አሠሪዎች፣ የትዳር ጓደኞች፣ ሠራተኞች … መጀመሪያ ራሳችሁን በሚገባ እወቁ፡፡ በተሰማራችሁበት ሁሉ ብቁ መሆናችሁን ገምግሙ ፤ ካልሆነ የአልቧልታ ወሬ በሰማችሁ ቁጥር ራሳችሁን እንደ ዛፍ እየገዘገዛችሁ በቁ እንቅልፍ በማጣት እሳት እንዳነሰው በቆሎ ስትገላበጡ ማደር ዕጣ ፈንታችሁ ይሆናል፤ ማህበራዊ ተራክቧችሁም ይደበዝዛል፡፡ ለጭንቀት ወለድ በሽታዎችና ለሞት ጥርጊያ መንገድ እያመቻቻችሁ መሆናችሁንም ቆም ብላችሁ ማጤን ይኖርባችሁዋል ፡፡ ስለዚህ ወሬኛ ሲመጣ ትልቅ የነቀርሳ በሽታ ይዞባችሁ መምጣቱን ተገንዝባችሁ ገና ማሞጥሞጥ ሲጀምር አፋን ትም ነው፡፡

**የወሬ**
**የለውም**
**ፍሬ፡፡**

# Edutainment

# አጫጭር ገጠመኞች

## አያድርስ

በአፄ ምኒልክ ጊዜ ነው። ንጉሥ ምኒልክ ከመሣፍንትና መኳንንት ጋር ስብሰባ ቢጤ ሊቀመጡ ነው። ስብሰባው በቅጡ ከመጀመሩ በፊት ታዲያ– ዛሬም ቢሆን ስብሰባ ስንጠራና ስንጠራ እንደምናደርገው ሁሉ – ከነዚሁ ባለሟሎቻቸው ጋር የማሟሟቂያ ወሬ ማውራት ይጀመራል። ከመሣፍንቱ መካከል ታዲያን አንዱ «እናንተ አሁን የምታስቡትን ዐውቃለሁ» ይልና ከንጉሡ በስተቀር ሁሉንም ያፋጥጣቸዋል። እነሱ ደግሞ፤ «እንዴ? ምን ችሎታ ቢኖርህ ነው የምናስበውን የምታውቀው? እንዴት ተደርጐ - አታውቀውም!» ይሉና ይሞግቱታል። እሱ ግን በዚያው ባሳቡ ይጠናና ወይ ፍንክች ያባ ቢላዎ ልጅ ይላል። እነሱም «በል እንግዲያውስ ንገረና - አሁን ምን እያሰብን ነው?» ይሉታል። እሱም ወዲያውኑ«ሁላችሁም የምታስቡት ስለንጉሣችን ስለ አፄ ምኒልክ ጤንነትና ዕድሜ ነው! አይደለም የሚል አለ?» ይላቸዋል። ማን ነው ወንዱ «አይ ስለንጉሣችን ዕድሜና ጤና አላስብም » የሚል! «ልክ ነህ ጌታው ! ዐውቀሃል ።» አሉትና «ተረቱለት»። /ተሸነፉለት ለማለት ነው/

ጨዋታው ቀጠለ ። በዚያው ስብሰባ ላይ አንድ ካህንም እንዳሉ ልብ ይሏል። አንድ ጉዳይ ይነሳል። «ማንም ሰው ሲጸልይ ቀጥ ብሎ ጸሎቱን አያደርስም፤ በጸሎቱ መሃል የሚያደናቅፈው ሃሳብ አይጠፋም። » የሚል ጨዋታ ይጀመርና ክርክሩ ይጦፋል ። «የለም ፤ እኔ ስጸልይ በጭራሽ የሚያናጥበኝ ነገር የለም። » ይላሉ ቄሱ ። ይሄኔ ንጉሡ «እስኪ አቡነ ዘበሰማያትን በነሲና ጸሎት ቀጥ ብለው ይውጡልኝ፤ እንዲያ ካደረጉ በቅሎየን ከነግላሷ እሸልምዎታለሁ።» ይላሉ። ቄሱም ተስማምተው ጸሎታቸውን ይቀጥላሉ። ጨረሱ። ንጉሡም ቀጠሉና አሉ። «በእርግጥ ምንም ሃሳብ ሳያናጥብዎ ጸልየው ጨረሱ? በእግዚአብሔር ስም ይምሉልኛል?» ብለው ካህኑን ባልጠበቁት ጥያቄ ያፋጥጧቸዋል። ቄሱም አሉ፤ «እርግጥ ነው– እየጸለይኩ እያለሁ– 'ንጉሡ እውነታቸውን ይሆን? በቅሎዋን ይሸልሙኝ ይሆን?' የሚል ሃሳብ ብልጭ ብሎብኝ እንደነበር አልዋሽዎትም።» ሃሳብና ቂም ይዞ ጸሎት - ሳል ይዞ ስርቆት ብለን ነባሩን ብሂል እናሻሽለው ይሆን?

ይሄኛው መርካቶ አካባቢ ነው። የተወሰኑ ሙስሊሞች በጋራ የዝሁር ሦላት እያደረሱ ነው። ባጠገባቸው ደግሞ አንድ ተንኮለኛ ቃልቻ ነበሩ። ሰዎቹ በተመስጦ ዱአቸውን ለአላህ በማቀበል ላይ እንዳሉ ቃልቻው ዝርዝር ሣንቲሞችን ይበትንና ሆን ብሎ ሆጭ የሚል ድምፅ እንዲሰሙ ያደርጋቸዋል። ይሄኔ ሁሉም ሦላት አድራሾች ሣንቲሞቹ ወዳንቃጨሉበት አቅጣጫ ዘወር ይላሉ –በደመነፍሳዊ ስሜት። ቃልቻውም አሉ – «ይሄን ዱአ እንኳንስ አላህ እኔም ብሆን አልቀበላችሁም።» ከልጅ ልጅ ቢለዩ ዓመትም አይቆዩ ይባል የለም? የነገር መመሳሰል ይሏል ይሄንን ነው ። የቄሱና የባለሦላቶቹ ዝክረ ነገር በአያሌው አልተመሳሰለብችሁም?

## ሚስተር ቢተር

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ነው። አንዲት 'የተዋጣላት' አልቃሽ ነበረች – ለጊዜው ወይዘሮ ዘለቃሽ እንበላት ስምዋን። እመት ዘለቃሽ በዚያን ጊዜ እስከ ሦስትና አራት መቶ ብር ነበር የምትጠይቀው ለአንድ ሙሾ። ለዕንባ ማፍለቂያና ለብርታት የሚቀርቡላት ምግብና ቢራ አይታሰብም። አንድ ወቅት ለውሎ ሊኮናተሯት ሰዎች ይመጣሉ። የደንቡን ሊከፍሏትም የቃል ውል አሥረው ይሄዳሉ ። ዘለቃሽ ወደሟች ስትሄድ የሞተው ሰው አበሻ ሳይሆን ፈረንጅ መሆኑ ይነገራታል ። ያኔ ውል ታፈርሳለች ። «የተስማማሁት አበሻ መስሎኝ እንጂ ፈረንጅ መሆኑን ባውቅ በዚህ ስለማያዋጣኝ አልስማማም ነበር» ብላ ድርቅ ትላለች። «የሞተው ሰው ነው፤ አበሻ ሆነ ፈረንጅ ምን ለውጥ አለው?» ብለው ሊያግባቡዋት ቢሞክሩም አልሆነም ። ወደ ዋጋ ድርድር ተገባ። «እና ስንት እንጨምር?!» ይሏታል፡፡ «መጨመሩን ምናምኑን ተውት። በአዲስ ውል አሥር ሺህ ብር ትከፍላላችሁ።» ትልና ክችች ትላለች – ማን? እመት ዘለቃሽ! ድርደሩ ጦፎ በወቅቱ አሥር ሺም ባይሆን በሆነው ዋጋ ተስማምተው ያስለቅሷታል ። የሚገርመው ከሰው ጠይቃ ሳይሆን አይቀርም

ሙሾውን በእንግሊዝኛ ማውረዷ ነው፤

ተቀበሉ አለች የከበቡዋትን አልቃሾች –ምን ብለው እንደሚቀበሉዋት ካስጠናቻቸው በኋላ ፤

**አልቃሽ** - ሚስተር ቢተር

**ተቀባይ** - ኢንተር ቱ ዘ ሶይል

**አልቃሽ** - ሚስተር ቢተር ኤ ጉድ ፓርፋዘር (ደጉ የደሃ አባት ለማለት ነው!)

**ተቀባይ** - ኢንተር ቱ ዘ ሶይል

**አልቃሽ** - ኃይሌ! (የሙሾ አዝማች ነው)

**ተቀባይ** - ኃይሌ፣ ኃይሌ!

በነገራችን ላይ በአሁኑ ዘመን የአስለቃሾች ሚና እየመነመነ መጥቶ አሁን አሁን ከነአካቴው በመክሰም ደረጃ ላይ ነው የሚገኘው። በዚያ ምትክ ይልቁንስ «ገንዘብ ካለ በሰማይ መንገድ አለ።» እንደሚባለው ገንዘብ ያለው ሚች ወይም ቀድሞ የተዘጋጀ ቤተሰብ ያለው ሰው ሲሞት በአስቀባሪ ድርጅቶች በክብር ታጅቦ በክብር ይቀበራል። ዕድር መግባት አለመግባት የማያሳስብበት ጊዜ ላይ ነን። ገንዘብዎን ይጭነቀው እንጂ አስከሬንዎን ግራና ቀኝ በልዩ አጀብ አንከብክበው ወደመቃብር ጉድጓድዎ የሚወስዱዎ አስቀባሪ ድርጅቶች እየተፈለፈሉ ነው - በጊዜዎ ለመሞት ያብቃዎ እንጂ።

## 'አላውቀውም' ወንጀል ነው?

በሀበሻ ምድር 'አላውቀውም' የምትለዋ ቃል በተለይ ዱሮ ዱሮ ውድ ነበረች፤ ለነገሩ አሁንም ሰማይ ላይ እንደተሰቀለች ናት።

አንድ ሰው ሲፈጠር ባዶ ነው፤ ራቁቱን ከባዶ ግን ቢማርና ቢመራመር ዕውቀትና ጥበብን በቀላሉ ሊቀስም ከሚያስችለው ጭንቅላት ጋር ወደዚች የተረገመችም ትሁን የተመረቀች ምድር ይመጣል። የሁሉም ዓይነት ልዩነቶች የሚፈጠሩትና ሰዎችን የሚለያዩት ከፍጥረት በኋላ በአካልና በመንፈስ እየታደገ ሲመጣ ነው።

የምናድግበት ባህልና ወግ፣ የቤተሰብ ዳራ ፣ የተፈጥሮ ዝንባሌ ፣ የትምህርት ሥርዓትና የመሳሰሉት ጉዳዮች በአዕምሮአዊ ይዞታችንና በስብዕናችን ላይ የራሳቸውን አሉታዊም ይሁን አወንታዊ ተፅዕኖ ማሳደራቸው ግን የታወቀ ነው። …

አንድ ሰው አንድ ነገር ሲጠየቅ የማያውቀው ከሆነ «አላውቀውም» ቢል የሞተ ያህል የሚሰማው ኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ ነው ቢባል ከእውነቱ ብዙም አልራቅንም። ማኅበረሰባችንን በተቻለ መጠን ጠጋ ብለን ለምናውቅ በተለይም በትምህርቱ ዓለም ጥርሳችንን የነቀልን ሰዎች በዚህ ረገድ በርካታ ግንዛቤ አለን።

ብዙና ብዙ ማለት ይቻላል ። ጥቂት አብነቶችን ብቻ በመጥቀስ ግን ይህን ጉዳይ እንዘምዝም።

አንድ የአማርኛ መምህር ናቸው ። ከተማሪዎቻቸው አንደኛው ክፍል ውስጥ የአንድን ቃል ትርጉም ይጠይቃቸዋል። ልጁ ተንኮለኛ ቢጤ ኖሯል። አስቀድሞ ለጓደኞቹ ነግሯቸዋል ምሥጢሩን። ያቺ ነገረኛ ቃል የኢትዮጵያ ቃል ሳትሆን ከሼክስፒር የተውኔት ድርሰቶች ውስጥ በአንደኛው የአንድ ገጸ ባሕርይ ስም ናት።

ተማሪ - ክፍል ውስጥ «ጋሼ – አንድ መጽሐፍ ሳነብ ያገኘሁትን ያልገባኝን አንድ ቃል ልጠይቅ?»

መምህር - «እንዴታ! ተማሪ ማለት እንደዚያም አይደል ታዲያ!

ተማሪ - «**ቲባልት** ምን ማለት ነው?»

መምህር - «አሃ - **ቲባልት** ማለት የመስቀል ወፍ የምትመስል በመፀው አካባቢ ብቅ የምትልና በወይና ደጋ አካባቢ የምትኖር የወፍ ዓይነት ናት።»

ይሄኔ ክፍሉ በሳቅ ይፈርሳል ። ተሜ ምሥጢሩን ቀድሞ አሾልኳላ! «ሁሉን አዋቂ» መምህርም አፍረው መሬቷ ብትውጣቸው በወደዱ።

በመሠረቱ የማናውቀውን ነገር አናውቀውም ማለት ጨዋነትና ብልህነት እንጂ የአላዋቂነት ወይም የደደብነት ምልክት አይደለም። አንድ ሰው ሁሉንም ነገር ሊያውቅ አይጠበቅበትም፤ ልወቅ ብሎ ከተነሳም ዕብደት ነው። የአዕምሮ የማወቅ ችሎታም ምንም እንኳን ገደቡ ይሄ ነው ተብሎ ባይነገርም ውስንነት እንዳለው መረዳት ለጤናማ ማኅበረሰባዊና ግለሰባዊ ግንኙነታችን አስተዋፅዖ አለው። ሁሉን እንደሚያውቅ ሰው ለማስመሰል ብንሞክርም ግብዝነት ነው። እርግጥ ነው ብዙ ነገር ማወቅ ይቻላል። ግን የምናውቀው ከማናውቀው መብለጡን የምናውቅ ብዙዎች አለመሆናችን ያሳዝናል። ይበልጥ የሚያስከፋው ነገር ደግሞ «አያውቅም» ላለመባል በምናደርገው ጥረት የማይሆን መልስ በመስጠት ሰዎችን የምናሳስት መብዛታችን ነው። የማናውቀው ነገር ሲገጥመን «ሰው ልጠይቅና እነግርሃለሁ፤ መዛግብትን ላገላብጥና መልሱን እሰጥሃለው፤ አብረን እናጠያይቅና ሌላ ጊዜ እንመለስበት፤ ይቅርታ ይህን ነገር አላውቀውም ስታውቀው ግን አደራ ለኔም አሳውቀኝ … » ማለትን ብንለምድ ለአወንታዊ ስብዕናችን የተሟላ ዕድገት ምንኛ በጠቀመን ነበር።

## የትርጉም ነገር

አንዱ ‹ምሁር› ከእንግሊዝኛ ወደ አማርኛ ትርጉም ለመተርጐም ይዋዋላል – ከአንዱ ድርጅት ጋር:: የሚተረጉመውን ዶክመንት ይረከብና «ተርጉሞ» ይመልሳል ፤ ክፍያውንም ይወስዳል:: ያ «የተተረጐመ» ዶክመንት ለተጨማሪ አርትዖት ለሌላ ሰው ይሰጣል። ያኔ እኔም ያን ዶኩመንት የማየት ዕድል ያጋጥመኝና አየዋለሁ ፤ ያሳዝናል የደረስንበት የዕውቀትና የግንዛቤ ደረጃ።

«Dray horse» የሚለውን እንደምን ብሎ እንደተረጐመው ከመግለጼ በፊት ተገቢ ትርጉሙን ልስጥ::

በእንግሊዝኛ ‹Dray horse› ማለት ወንበርና ክፈፍ የሌለው በፈረስ ወይም በአህያ የሚጎተት የዕቃ ጋሪ ማለት ነው:: ያ ሰውዬ ግን ‹ደረቅ ፈረስ› ብሎ ነው የተረጐመው :: በዚህ አጋጣሚ ስንትና ስንት የትርጉም ሥራዎች እየተበላሹ ወደተጠቃሚዎቻቸው እንደሚሄዱ መገመት ይቻላል፡፤ ይህ ሁኔታ የሚያሳየው “ተርጓሚው“ ሰውን ጠይቆ ለመረዳት ወይም መዛግብትን አገላብጦ ግንዛቤ ለመጨበጥ ምንም ፍላጐት የሌለው መሆኑን ነው:: ምናለ መዝገበ ቃላት ቢያይ? ምናለ ሰው ቢጠይቅ? አ - አ ሰው ከጠየቀማ “አላዋቂ» ሊባል ነው:: አለማወቅን እንዳለማወቅ ያለ የከፋ ነገር ደግሞ የለም:: መጠየቅ ወንጀል አይደለም:: ለማወቅ ሲባል ከሰማይ በታች ከምድር በላይ ያሉ ዘዴዎችን ሁሉ መጠቀም ብልህነት እንጂ ቂልነት አይደለም:: በዕውቀት የበለጸጉ ፈላስፎች አንድን ነገር ለማወቅ ከሕጻናትና ከእንስሳት ሳይቀር በትህትና ዝቅ ብለው ይጠይቃሉ ፤ ይማራሉ:: ጥሬና ብስል የሆነው አብዛኛው ፊደል ለይቶኣል የሚባለው የሀገራችን ሰው ግን በሀፍረት አቡጀዲ ተጀቡኖ በውሸትም አዋቂ መስሎ ይኮፈሳል እንጂ አዲስ ነገር ለማወቅ ያለው ጉጉትና ፍላጐት በእጅጉ ዝቅተኛ ነው:: እርግጥ ነው የሚያውቁትን በከንቱ የማይዘላብዱ የማያውቁትን በአግባቡ የሚያሳወቁና ደርዝ ያለው ስብዕና ያላቸው ዘመናዊ የሀበሻ ምሁራን የሉም ማለት አይደለም:: አሉ ግን ቁጥራቸው የሚያበረታታ ለመሆን ገና ጥቂት ጊዜ ይቀራል::

እንደማሳረጊያ መልዕክት፤ – የማናውቀውን ነገር ከመጠየቅ አንቦዝን:: በገበያ፣ በምግብ ቤት፣ በትምህርት ቤት ፣ ብቻ በየትም ሥፍራና ሁኔታ የማናውቀው ነገር ሲገጥመን በግልጽ እንጠይቅ :: ቀላል ጥያቄም ቢሆን አንፈርበት:: በጥያቄያችን ሰዎች ሊስቁ ቢችሉ እንኳን ጥርሳቸውን ተነቅሰው ይሳቁ:: እኛ ግን እንጠይቅና ዕንወቅ:: የሚያሳፍረው ለመጠየቅ ማፈር ራሱ እንጂ ጠይቆ ማወቅ አለመሆኑን እንረዳ:: ለመጠየቅ በማፈራችን ምክንያት ከሚደርስብን ችግር ይልቅ ባለመጠየቃችን ሊደርስብን የሚችለው ጉዳት በጣም ይበልጣል:: ጠይቆ መረዳት የአስተዋይነትና የብስለት ምልክት እንጂ መበለጥ አለመሆኑን እንገንዘብ::

## ከእንግዲህ ኩላሊት

በዘመነ ንጉሥ ኃይለ ሥላሴ የመጀመሪያዎቹ ዓመታት በአዲስ አበባ ውስጥ “ምርጥዋ” የሚባል ታዋቂ አዝማሪ ነበር:: አዝማሪው በነበረበት በዚያን ዘመን በሠርግም በመልስም በልዩ ልዩ የደስታ ግብዣዎችም እየተጠራ ህዝብን የሚያዝናና ስመጥር አዝማሪ ነበር - ምርጥዋ::

አንዲት ክፉ አጋጣሚ ግን የምርጥዋን ሕይወት በቅጽበት ቀጠፈቻት:: በዚያም ሳቢያ እንዲህ ተገጠመ፤

ከእንግዲህ ኩላሊት ማንም አይበላሽ፣
የሕዝቡን አጫዋች ምርጥዋን ገድለሽ::

እንዲህ የተገጠመው ምርጥዋ የሞተው በአንዲት ያልተባረከች አጋጣሚ የኩላሊት ሥጋ ሲበላ የሥጋዋ ሥር ከጥርሱ አልተላቀቀች ኖሮ ጉሮሮው ውስጥ ተሰንቅራ አንቃ ስለገደለችው ነበር:: ምናለ ጀርባውን በቡጢ ቢደልቁት ኖሮ? ለነገሩ የተቆረጠችን ነፍስ ማን ሊቀጥል ይቻለዋል? ዋናው ሰኞን አያድርግ ነው::

## ፍትሕ ርትዕ

ፍትሕና ርትዕ የሚባሉ የሕግ ቃላት አሉ:: የፍትሕ ኀልውና የትም ቦታና በየትኛውም ሁኔታ ወሳኝ ነው:: የርስዋ መጥፋት ወይም መንሻፈፍ ነው – እንደሚባለው ከሆነ – የዓለምንም ወቅታዊ ቆርፋዳ መልክ ሊያሰጥ የቻለው:: ፍትሕ ካለች ሁሉ ነገር አለ:: ፍትሕ ከሌለች ሁሉ ነገር የለም – አንድ ነገር ግን አለ – ያም የፍትሕ አለመኖርና እርሱንም ተከትሎ ሊመጣ የሚችለው ወልጋዳ ነገር ሁሉ::

ፍትሕ የት ይጀምራል? ፍትሕ ቤት ውስጥ ይጀምራል:: በቤት ውስጥ ልጆች ቢኖሩን ሁሉንም እኩል ነው ማየት ያለብን:: እኩል መንከባከብ፣ እኩል መውደድና፣ እኩል መጨነቅ ወዘተ:: ለአንዱ በተለየ የተለየ ስሜት ካለን ፍትሕ ተዛባ፣ ርትዕ ጠፋች:: ፍርድና ብያኔን ለሁሉም በምንሰጥበት በማናኛውም ጉዳይ ፍትሕ ወሳኝ ናት:: ልጃችን ስለሆነ ፣ ባለቤታችን ስለሆነ፣ ባለቤታችን ስለሆነች፣ ጐረቤታችን ስለሆነ … ፍርድን ብናጣምም፣ ፍትሕን ብናዛባ አለቀልን፤ የፍትሕ ርትዕን ዓይን ጓጐጥን ማለት ነው:: የዞረ ድምሩ ውጤት ደግሞ ለኛም አይቀርልንም::‹በሠፈሩት ቁና መሠፈር አይቀርም› ነው ነገሩ:: አንድ በቅርብ የማውቃቸው መምህር ነበሩ:: በሚሠሩበት ትምህርት ቤት የቤተ ሙከራ ክፍል ኃላፊ ናቸው::አንድ የትምህርት ዓይነት ያስተምራሉ:: በሚያስተምሩት ክፍል ውስጥ የርሳቸውም ልጅ ይማራል:: ፈተና ሲኖርም ሆነ ሳይኖር በዚያ ትምህርት ያ ልጃቸው ከማንም ልጅ የተለየ ጥቅምም ሆነ ጉዳት አያገኝም:: እዚህ ላይ ለልጁ ቀርቶ ለዘመዱና ለወዳጁ ልጅ በተለያዬ መልክ አድልዎ ሊያሳይ የሚችል ቀድሞውን በእናቱ ማሕጸን ውስጥ

ውኃ ቢቀር የሚሻለው "መምህር " ሊኖር እንደሚችል መዘንጋት አይገባንም ። ስንትና ስንት ነገር ስናዉቅ?

በአንድ ወቅት እኚህ መምህር ዋና ፈተና ይሰጣሉ። የአንደኛዋ ጥያቄ መልስ "D" ነው። የልጃቸውን ወረቀት ሲያርሙ ጎሊናቸውን የሚያወዛግብ ክስተት ይገጥማቸውል። ያም ምንድነው ልጁ የጻፈው መልስ ‹B› ይሁን 'D' መለየት ያቅታቸዋል። ብዕሩ እያቆራረጠበት በደንብ ሳይጽፍ ቀርቶ መልስ ብሎ የሰጠው ‹B› ከ 'D' ጋር የመመሳሰል ጠባይ አሳየ። 'B' ውስጥ ያለችው የመሃከለኛ መስመር በጉልህ አትታይምና 'D' የመምሰል አዝማሚያ ታሳያለች። ልጁን ጠርተው ጠየቁት።" "B" ብዬ ነው መልስ የሰጠሁት" ይላቸዋል። እሳቸው ግን 'X' ለማድረግ ክፉኛ ተቸገሩ ። "ምናልባት 'D' ብሎ መጻፉን ረስቶት ከሆነስ ? ልጅ ነው ቶሎ ይረሳል" ብለው ይጨነቃሉ ። እናም ምን አደረጉ በቤተ ሙከራው ማይክሮስኮኘ ላይ የልጁን የመልስ ወረቀት እንደ ሞተች ዝንብ ዘርግተው ይመለከታሉ። ያኔም የተልኮሰኮሰችዋ መስመር ቁልጭ ብላ ትታያቸውና አሳምረው 'X' ኣቸውን ያስቀምጡለታል። አባት ማለት እንዲህ ነው። ቀጭን ምክንያት ፈልጐ አሳግባብ ልጅን ከመጥቀም ይልቅ በሳይንሳዊ መሣሪያም ቢሆን ታግዞ ፍትሕን ማስጠበቅ ኀሊናዊም ሃይማኖታዊም ነው። ደስ አይልም አንባቢያን?

## ቀልድ የሚመስል ገጠመኝ

በቅርቡ መገናኛ አካባቢ በሚገኝ አንድ መብራት ማቋረጫ ላይ አቋርጣለሁ። እኔ ከተሻገርኩ በኋላ አንድ ጓደኛዬን አይቼ እየጠበቅሁት ሳለሁ አንዲት አሮጊት ወደዜብራው ማቋረጫ መንገድ ይገባሉ። ያኔ አንድ ቀልቃላ የሚኒባስ ታክሲ ሹፌር ሊገጫቸው ሲል ፍሬኑን ሲጢጥ አድርጐ ለጥቂት ያድናቸዋል። ሴትየዋም በድንጋጤ ክው ይላሉ። ሁላችንም ደነገጥን።

አሮጊቷ ከድንጋጤያቸው ከተረጋጉ በኋላ የተናገሩት ግን ባካባቢው የነበርነውን ሁሉ አሳቀን። "አንተ! ይሄ የእናትህ ንቅሳት መሰለህ? አስተውለህ አትነዳም? ባለጌ ስድ" አሉት። ሲያንሰው ነው። ምን አንቀዠቀዠው! እሳቸው ግን ከአደጋው መትረፋቸው ይበቃቸው ነበር። በስድቡ ምርቃት እኔም ደስ አላለኝም።

---

<u>**Cows & Politics Explained**</u>

***A CHRISTIAN DEMOCRAT:*** ***You have two cows. You keep one and give one to your neighbor.***

***A SOCIALIST:*** ***You have two cows. The government takes one and gives it to your neighbor.***

***AN AMERICAN REPUBLICAN:*** ***You have two cows. Your neighbor has none. So what?***

***AN AMERICAN DEMOCRAT:*** ***You have two cows. Your neighbor has none. You feel guilty for being successful. You vote people into office who tax your cows, forcing you to sell one to raise money to pay the tax. The people you voted for then take the tax money and buy a cow and give it to your neighbor. You feel righteous.***

***A COMMUNIST:*** ***You have two cows. The government seizes both and provides you with milk.***

***A FASCIST:*** ***You have two cows. The government seizes both and sells you the milk. You join the underground and start a campaign of sabotage.***

***DEMOCRACY, AMERICAN STYLE:*** ***You have two cows. The government taxes you to the point you have to sell both to support a man in a foreign country who has only one cow, which was a gift from your government.***

***CAPITALISM, AMERICAN STYLE:*** ***You have two cows. You sell one, buy a bull, and build a herd of cows.***

***BUREAUCRACY, AMERICAN STYLE:*** ***You have two cows. The government takes them both, shoots one, milks the other, pays you for the milk, then pours the milk down the drain.***

***AN AMERICAN CORPORATION:*** ***You have two cows. You sell one, and force the other to produce the milk of four cows. You are surprised when the cow drops dead.***

***A FRENCH CORPORATION:*** ***You have two cows. You go on strike because you want three cows.***

***A JAPANESE CORPORATION:*** ***You have two cows. You redesign them so they are one-tenth the size of an ordinary cow and produce twenty times the milk. You then create clever cow cartoon images called Cowkimon and market them World-Wide.***

***A GERMAN CORPORATION:*** ***You have two cows. You reengineer them so they live for 100 years, eat once a month, and milk themselves.***

***A BRITISH CORPORATION:*** ***You have two cows. They are mad. They die. Pass the shepherd's pie, please.***

***AN ITALIAN CORPORATION:*** ***You have two cows, but you don't know where they are. You break for lunch.***

***A RUSSIAN CORPORATION:*** ***You have two cows. You count them and learn you have five cows. You count them again and learn you have 42 cows. You count them again and learn you have 12 cows. You stop counting cows and open another bottle of vodka.***

***A SWISS CORPORATION:*** ***You have 5000 cows, none of which belong to you. You charge others for storing them.***

***A BRAZILIAN CORPORATION:*** ***You have two cows. You enter into a partnership with an American corporation. Soon you have 1000 cows and the American corporation declares bankruptcy.***

***AN INDIAN CORPORATION:*** ***You have two cows. You worship both of them.***

***A CHINESE CORPORATION:*** ***You have two cows. You have 300 people milking them. You claim full employment, high bovine productivity, and arrest the newsman who reported on them.***

AN ISRAELI CORPORATION: ***There are these two Jewish cows, right? They open a milk factory, an ice cream store, and then sell the movie rights. They send their calves to Harvard to become doctors. So,*** **who** ***needs people?***

## ለዕረፍት ጊዜዎ

ከዚህ በታች በፈረንጅኛ የተሰጡትን አባባሎች እንደነገሩም ቢሆን ወዳማርኛ ሊተኩ የሚችሉትን ከሥር ከተሰጡት የአማርኛ ብሂሎች በመምረጥ ያዛምዱ:: (መልሱን በዚሁ ዕትም ውስጥ ባንደኛው ገጽ ላይ ይመልከቱ::

1. A day in prison is longer than a thousand years at large.
2. A beggar who begs from another beggar will never get rich.
3. A cat may look at a king.
4. A bad workman always blames his tools.
5. A bird in the hand is worth two in the bush.
6. A burned cat shuns the fireplace.
7. A cask of wine works more miracles than a church full of saints.
8. A clever doctor never treats himself.
9. A disease known is half cured.
10. A donkey is a donkey though it may carry the Sultan's treasure.
11. A drowning man grasps at water.
12. A constant guest is never welcome.

(Anonymous Sayings taken from Microsoft, Encarta 2009)

1. **የጨነቀው እርጉዝ ያገባል፤ የባሰበት እመጫት::**
2. **ዋጮን ቢገለብጡት ያው ዋጮ ነው::**
3. **በሽታውን የደበቀ መድሐኒት አይገኝለትም::**
4. **የጭንቅ ሌሊት አይነጋም::**
5. **የማትወደው እንግዳ ቤትህ ሲመጣ ቤት መጥረግ ጀምር::**
6. **ሞኝ አሳላፊ ዘመዱን ይበድላል::**
7. **ልብ እንቅርት ይመኛል::**
8. **ሆድ ያባውን ብቅል ያወጣዋል::**
9. **እባብ ያዬ በልጥ በረዬ::**
10. **ከእጄ በጉንጬ::**
11. **የእናቴ መቀነት አሰናከለኝ::**
12. **የለማኝ ሥልቻ ቢንከባለል እለማኝ ደጅ አረፈ::**

## The Overseslf

A baby within its mother dies to that warm, comfortable life within, and reluctantly emerges into the cold, hard world without. Birth pangs are death pangs, death to the old, birth into a new state. A person dies upon Earth and the pains of death are the pains of birth into a different state of existence. Most times death—death itself—is a quite painless process. Actually, as death approaches, Nature, in the shape of various metabolic changes, introduces a form of anesthesia into the body system, anesthesia which culls the actual perceptions while allowing the body reflexes to make certain movements which people think of as death pains. People actually associate pain and death, or if you prefer, death and pain, because in the majority of cases people who are grievously ill die apparently in pain, but that pain, remember, is not the pain of death but

the pain caused by the illness itself. Perhaps there is a cancer, something affecting body organs, grasping at nerve endings or eating them away. But let us remember that this pain is the pain of the illness, the pain of the complaint, not death itself. Death, the actual state of transition from this world to the next, the actual state of leaving this physical body, is a painless process because of the anesthetic properties which come to most bodies at the moment of death. Some of us know what it is to die and to remember everything, and to come 120 back still remembering. In the process of dying we have a body which is ailing, functions are failing. But remember this, the functions are failing, that means the ability to perceive or apperceive or to comprehend pain impulses is failing also. We know that people sometimes give an impression of pain at dying, but this again is an illusion. The dying body is a body which has usually (except in the case of accident) reached the end of its endurance, it can go no more, the mechanism is failing, there is no longer the ability for metabolic processes to renew failing organisms. Eventually the heart stops, the breathing stops. Clinically a person is dead when no breath condenses on a mirror held before the lips; clinically and legally a person is dead when there is no longer a pulse or a heart-beat. People do not die on the instant, however. After the heart has ceased to beat and after the lungs have ceased to pump, the brain is the next to die. The brain cannot live long without its precious supply of oxygen, but even the brain does not die instantly, it takes minutes. There have been absolutely authenticated cases where people have been beheaded, and the head, severed from the body, has been held up for public inspection. The lips have continued to move and a lip reader can distinguish the words being formed. Obviously only a lip reader can interpret what is being said because there can be no speech when the neck has been cut and the supply of air from

the lungs terminated. It is the air supply going past the vocal chords which makes the sound. After the brain has died, after the brain is no longer capable of functioning through this lack of oxygen, the rest of the body dies slowly. Various organs die throughout a day or so. At the end of three days the body is just a lump of decomposing protoplasm, but the body does not matter, it is the immortal soul that matters—the **Overself**.

T. Lobsang Rampa, **Chapters of Life**, pp.120 - 123

# ልብ ወለድ

## እውነትና ፀሐይ

**ደራሲ ፣** R.K. Narayan
**ምንጭ፣** Fundamentals of Literature,
Berhanu Matthews, PhD, 2009, (pages 165-171)
**ትርጉም፣** ፋንታ አያሌው፣ ቅ/ማ/ዩ/ኮ

'እውነት እንደ ፀሐይ ናት' አለ ሴክሃር የፀሐይን ዓይን ማጥበርበርና የእውነትን መራርነት በንጽጽር አጉልቶ ለማሳየት፡፡ ሴክሃር ቀጠለ - ማንም ይሁን ማን ካለአንዳች አጋዥ መሣሪያ ፀሐይን በቀጥታ በዓይኑ ሊያይ የሚችል ሰው ይኖራል ብዬ አልገምትም፡፡ ቢሞክር እንኳን ጨረሯ ዓይኑን ያጥበረብረዋል ወይም ያልታሰበ ጉዳት ሊያስከትልበት ይችላል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ሰዎች እውነትን በእውነትነትዋ ላለመቀበል በመፈለግ ከጧት እስከ ማታ እንጼቱን ያህል በውሸት መርዝ ሲበክልዋት እንደሚውሉ ለአፍታ ያህል ታሰበው፡፡ የዛሬዋን ዕለት ደግሞ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ እውነትን ሊጋፈጣት ወደደ፡፡ ቢያንስ በዓመት አንዲት ቀን እንዲያው ለአንድ ጀምበር እውነትን እንዘክራት አለ፡፡ ስለ እውነትም መክፈል የሚገባንን መስዋትዕነት ሁሉ ልንከፍል እንደሚገባ ሴክሃር ውስጡን አሳመነ፡፡ አለበለዚያ በውሸት መኖር ትርጉም አልባ ነው፡፡ ይህች የዛሬዋ ቀን ለሴክሃር ልዩ ቀን እንደምትሆን ገመተ- እውነትን በጥሬዋ ሳትሸፋፈን እንዳለች የሚያንፀባርቅባት ቀን፤ አስፈላጊ ሆኖም ከተገኘ እውነትን በመናገሩና በይሉኝታም ይሁን በፍርሀት አንድን ነገር አደባብሶ ወይም ተቅጠፍጥፎ ባለማለፉ ሊደርስበት የሚችለውን እንግልትና መገለል ሊቋቋም ለራሱ ቃል ገባ፡፡ ይህን በራሱ ሕይወት እውነተኝነትን የማየት ሙከራ ለማንም ሌላ ሰው አልተናገረም – ለቤተሰቡ እንኳን! ይህን ሙከራውን ሊያደርግ ያቀደው ምሥጢራዊነቱን በራሱና በፈጣሪው መካከል ብቻ ጠብቆ ነው፡፡

የመጀመሪያው ፈተና የተከሰተው ገና በማለዳ እገዛ ቤቱ ውስጥ ነው፤ እስከዚያች ዕለት ድረስ «ጣት ያስቆረጥማል» እያለ በሚያሞካሸው ቁርስ ላይ ነው ቀዳሚውን የእውነትን ዘገር የወረወረበት፡፡ ባለቤቱ ጉሕ ሳይቀድ ጀምራ ስትደክምበት የባጀችውን ባህላዊ ቁርስ ገና መቅመስ ከመጀመሩ ፊቱን ኮሰኮሰበት - ሴክሃር፡፡ ያልተለመደ ባሕርይ ያየችበት ባለቤቱ "ምን ሆነሃል? አይጣፍጥም?" በማለት የጠበቀውን ጥያቄ ወረወረችበት፡፡ መልሱም «ግሩም ነው የኔ ፍቅር፤ ጥፍጥናው ልዩ ነው፤እጅ ያስቆረጥማል»፡፡ እንደሚሆን ሳትጠብቅ አልቀረችም፡፡ ወይም ቢያንስ «አይ፤ ጥሩ ነው ግን ለጊዜው አላሰኘኝም፤ በቃኝ» ሊላት እንደሚችል ጠብቃለች፡፡ ሴክሃር ግን የተለየ መልስ ነበረው፡፡ የእውነት የብርሃን ጨረር እንደፀሐይ ጨረሮች አእምሮን የሚወጋ ቢሆንም ያን ተቋቁሞ «በጭራሽ አይጣፍጥም፤ ከጉሮሮዬም ሊወርድልኝ አልቻለ፤ አዝናለሁ» አላትና አረፈው፡፡ ያስደነግጣል፡፡ የተናገረው እውነት የባለቤቱን ስሜት ምን ያህል ሊጎዳ እንደሚችል እያሰላሰለና የፊቷ የብርሃን ፀዳል በአንዴ መደብዘዙን እየተመለከተ እራሱ ለራሱ «ምንም ማድረግ አልችልም» አለ፤ እውነት እንደ ፀሐይ ናት፡፡

የሚቀጥለው ሙከራው ደግሞ መሥሪያ ቤት ሲደርስ የገጠመው የአንድ ጓደኛው ዜና ዕረፍት ነው፡፡ የመምህራን ማረፊያ ስታፍ ውስጥ ከተቀመጡት መምህራን አንደኛው «ሴክሃር - እንትና መሞቱን ሰማህ? አያሳዝንም ትላለህ?» ሲለው ሴክሃር ከወትሮ ባሕርይው በተለዬ ትንሽ እንኳን ሳያቅማማ «ምኑ ነው የሚያሳዝነው? በጭራሽ አያሳዝንም፤ እንዲያውም ጥሩ ነገር ነው!» አለው፡፡ ሌላው መምህር ቀጠለ «እንዴ ምን ነካህ? ጥሩ ሰው እኮ ነበር፡፡ በዚያ ላይ ...» ሴክሃር አላስጨረሰውም ቢያንስ ይህችን ቀን ስለ እውነት እውነትን ብቻ ሊናገር በራሱ ምሎ ተገዝቷልና «ምን ማለታችሁ ነው? ሰውየው እንደምትሉትና ልትሉለት እንደምትችሉት ሁሉ ደግና ሩህሩህ ሰው አልነበረም፡፡ በሚገባ አውቀዋለሁ፤ ዋሾና ለቸገረው ዱዲ እንኳን የማይደማው ቆጥቋጣ ነበር፡፡ በዚያም ላይ አውሬ ቢጤ ጨካኝ ሰው ነበር፡፡ ይህ ዓይነቱ ሰው ቢሞት ግልግል እንጂ የምን ሙሾና ደረት መምታት ነው? ማለባበሳችሁን ተውትና ይልቁንስ አገር የሚያውቀውን እውነት በድፍረት ተናገሩ፡፡»

አለና አፋቸውን አስያዛቸው፡፡ ቀኒቷን ለእውነት መታሰቢያነት ሊያውላት ከጧቱ ዝቷላ!

ሴክሃር በሚሠራበት ትምህርት ቤት የጂኦግራፊ መምህር ነው፡፡ በመጨረሻዋ ክፍለ ጊዜ የተማሪዎች መለቀቂያ የመጨረሻ ደወል አካባቢ ከትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር የተላከና በቁራጭ ወረቀት ላይ የተጻፈ ማስታወሻ ደረሰው፡፡ «ለጥብቅ ጉዳይ ስለምፈልግህ ወደ ቤትህ ከመሄድህ በፊት እባክህ ላግኝህ» ይላል የት/ቤቱ ርዕሰ መምህር አጭር ሬኮማንዴ፡፡ ሴክሃርም አለ «አይይ! ጊዜ አጥቼ ሳላርማቸው ስለቀረሁት ስለነዚያ ጣጠኛ የፈተና ወረቀቶች ሊያነጋግረኝ ፈልጐ መሆን አለበት፡፡" እንደ ጦጣ ጫጭረው የሰጡትን የመቶ ተማሪዎች የፈተና ወረቀት አንብቦ ለማረም ሞት ሞት እየመሰለው ሳይነካቸው ጥቂት ሳምንታት አልፈዋል፡፡

ደወሉ ተደወለ፣ተማሪዎችም ከት/ቤቱ ቅጽር ግቢ እየወጡ በየፊናቸው ወደየቤታቸው መሄድ ጀመሩ፡፡ ሴክሃር በቀጥታ ወደ ርዕሰ መምህሩ ቢሮ አመራ፣ የቢሮውን በር አንኳኩቶ ከመግባቱ በፊት ቆም ብሎ የኮቱን አዝራር አስተካክሎ ቆለፈ፡፡ ይህን ያደረገው ርዕሰ መምህሩ ወግ አጥባቂ ቢጤ በመሆናቸው በዝርክርክነትና በአለባበሱ ግዴለሽነት እንዳይታዘቡት ለመጠንቀቅ ነው፡፡

ትህትና በተሞላበት ሁኔታ «ጤና ይስጥልኝ ጌታዬ!» አለና ወደተጠራበት ቢሮ ገባ፡፡ ርዕሰ መምህሩ ፈገግታ ባልተለየው ወዳጃዊ ስሜት የአጸፋ ሠላምታውን ከሰጡት በኋላ «የዛሬን ምሽት ለአንድ ጉዳይ ፈልጌህ ነበር፣ ነጻ ነህ? ማለት… ትችላለህ?» አሉት፣ ከጠበቀው ውጪ፡፡ ሴክሃርም አለ «አይ… እንዲያው ወጣ አድርጌ አንሸራሽራችኋለሁ ብዬ ለልጆቼ የገባሁት ቃል እንጂ ሌላ ጉዳይ እንኳን የለኝም፡፡» «አሃ! እንዲያ ከሆነ መልካም፡፡ ልጆቹን ሌላ ቀን ታንሸራሽራቸዋለህ፣ ለዛሬ በቤቴ የኔ እንግዳ ትሆናለህ…፡፡»

«ጥሩ … እንዳሉት ይሁን ጌታዬ … እሺ …» አለና «ምን የተለዩ ነገር አለ ቤትዎ? ማለቴ በደግ ፈለጉኝ?» ሲል ፈራ ተባ እያለ የተፈለገበትን ጉዳይ ለማወቅ በትህትና ጠየቀ፡፡ መቼስ የ 'አለቃ ት'ዛዝ' አይደል?

ርዕሰ መምህሩም ሥጋቱን ተረዱና «አዎ፣ ሴክሃር በሙዚቃ ደካማ መሆኔን መቼም ታውቃለህ አይደል?» አሉት አሁንም በፈገግታ፡፡

«እንዴታ፣ በሚገባ አውቃለሁ እንጂ ! ጌታዬ»

እናልህ እስካሁን ለብቻዬ ስማርና ብቻዬን ስለማመድ ከርሜያለሁ፣ ዛሬና በዚህች ምሽት ግን አንተ ጥሩ የሙዚቃ ችሎታ እንዳለህ ስለማውቅ በደንብ አድምጠህ እንድትገመግመኝ እፈልጋለሁ፡፡ እንዲያጅቡኝ ከበሮ መቺና ቫዬሊን ተጫዋቾችም አዘጋጅቻለሁ፡፡ በዚህ መልክ በተሟላ የሙዚቃ ባንድ የሙዚቃ ዝግጅት ሳደርግና የሙዚቃን ጣዕም አዋቂ ሰው ለግምገማ ስጋብዝ የመጀመሪያዬ ነው፡፡ የተሳካ ሥራ እንደሚሆንልኝ ቅንጣት ጥርጣሬ የለኝም፡፡

እውነት ነው—ሴክሃር ከመምህርነት ሙያው በተጓዳኝ የሙዚቃ ችሎታንና የሙዚቃ ሥራን አብጠርጥሮ በመለየት ማለፊያውን ከእንቶፈንቶ ለመለየት ያለው ተሰጥዖ እንከን አይወጣለትም፡፡ በከተማው ውስጥ ከሚገኙ ጥቂት የሙዚቃ ሃያሲያን መካከል ሴክሃር አንዱ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ችሎታው በርዕሰ መምህሩ ዘንድ ታውቆ ለዚህ አጣብቂኝ የሕይወት ፈተና ይዳርገኛል ብሎ አስቦ አያውቅም - በጭራሽ፡፡ የፊት ገጽታውን አጢነው ፣ «ዱብ ዕዳ ነገር ሆነብህ አይደል?» አሉት ርዕሰ መምህሩ፡፡ ቀጥሎም «በሬን ዘግቼ ይህ ነው የማይባል ሀብትና ንብረቴን ነው የከሰከስኩበት - ለሙዚቃ ፍቅር፣ በሙዚቃ ፍቅር፣ ስለሙዚቃ ፍቅር ስል፡፡»

ሁለቱም ተያይዘው ወደ ርዕሰ መምህሩ ቤት ገቡ፡፡ ወደ ውስጠኛው የቤቱ ክፍል በሚያመሩበት ወቅት «እንደምታውቀው ፈጣሪ የልጅ ፍሬ ነስቶኛል፣ ወልጄ አልሳምኩም፣አሳድጌ አልዳርኩም፡፡ ለዚህ ብሶቴ ማካካሻ ግን የሙዚቃን ፍቅርና የመጫወት ጥበብ አይከለክለኝም ብዬ አምናለሁ፡፡» አሉ ሀዘን ባጠላበት የንግግር ድባብ፡፡ በማከልም ርዕሰ መምህሩ የሕይዎትን መሰላቸት ለመግፈፍና አዕምሮአቸውን ለማደስ ወደ ሙዚቃ ዓለም እንዴት እንደተሳቡ፣ በመጀመሪያ አካባቢ የሙዚቃ መምህራቸው በችሎታቸው ላይ እንዴት እንዳላገጠባቸውና ተስፋ ሊያስቆርጣቸው እንደሞከረ በሂደት ግን ተስፋ ያላቸው መሆናቸውን እንደገለጸላቸው፣ ያም ተስፋና ምኞት ደስታ የሸሸውን ሕይወታቸውን ለመደበቅና ለመርሳት እንዴት ሊጠቀሙበት እንደፈለጉ በዝርዝር አጫወቱት፡፡

ርዕሰ መምህሩ ሴክሃርን ለማግባባትና የግምገማው ውጤት ወደርሳቸው ባጋደለ መልኩ የተሳካ እንዲሆን በሀር ጨርቅ በተለበጠ ልዩ የእንግዶች ወንበር ላይ አስቀመጡት፣ ለመክሰስ የሚሆኑ ጣፋጭ ምግቦችን አስመጥተው ጠረጴዛው ላይ ኮለኮሉ፣ በጥቅሉ የልጃቸው ባል አማቻቸው ከነሚስቱ በእንግድነት የመጣ ያህል ይመስላል መስተንግዶው፡፡ ቀጠሉናም «አዬህ ፣ ሙዚቃዬን በጥሞናና በነፃ አዕምሮ ልታዳምጥና ፍርድህን ልትሰጥ ይገባል፡፡ ስለነዚያ የተማሪዎች ፈተናም በፍጹም አትጨነቅ፣

አንድ ተጨማሪ ሳምንት ሰጥቼሃለሁ።» አሉት ፈገግታ በተመላበት ልዩ ቅላጼ።

ሴክሃር በደስታ ተዋጠ። የተሰጠውን የአንድ ሳምንት የፈተና ማስገቢያ ጊዜም በነካ አፋቸው ወደ ሁለት ሳምንት እንዲገፉለት ጠየቀ፤ አልተከለከለም-ተፈቀደለት። ምክንያቱም ለታላቁ የተናጠል «አይዶል ሾው» ገምጋሚነት ታጭቶና ተመርጦ በዳኝነቱ ችሎት ላይ ተሠይሚልና። በተፈቀደለት አሥር ቀናት ውስጥም በቀን አሥሩን በቀይ ብዕሩ እየቀነደበ መቶውን በአሥር ቀናት ውስጥ አርሞ ሲያጠናቅቅ ያኔውኑ ታየው፤ በዚያውም ከወቀሳና ከቅጣት ሲያመልጥ ወዲያውኑ ታሰበው።

ታምቡረኛውና ሻዮሊኒስቱ ቦታ ቦታቸውን ያዙ። ድምፃዊው ርዕሰ መምህርም በመሃላቸው ተሰየሙ። የሚጠበቀው የሴክሃር ተረጋግቶ መቀመጥና የሙዚቃው መጀመር ነው። ሁሉም እንደታሰበው ሆነ። ድምፃዊው ልክ እንደኘሮፌሽናል ዘፋኝ በሁለቱ የሙዚቃ መሣሪያ ተጫዋቾች መሃል ቆመው ጉሮሮአቸውን ከጠራረጉ በኋላ ዘፈኑን በሥልት ያስነኩት ጀመር። በጀመሩት ሥልት ጥቂትም ሳይሄዱ አቋረጡና መላ ትኩረታቸውን ወደ ሴክሃር በማድረግ «እንዴት ነው ቆንጆ እዘፍናለሁ?» አሉና ጠየቁ። ሴክሃርም ያልሰማ በመምሰል ጥያቄውን የጐንዮሽ ተወና ዘፈኑን እንዲቀጥሉ ባገጩ አመላከታቸው። ርዕሰ መምህሩ ዘፈናቸውን በደስታ ቀጠሉ። አንዱን እንደምንም ጨረሱ። ሌሎች ሁለት ዘፈኖችንም ከተለያዩ ዕውቅ ድምፃዊያን በመኮረጅ አቀነቀኑ። ሰውዬው መዝፈን ከጀመሩበት ቅጽበት አንስቶ ግን ሴክሃር በውስጡ «ምን እንደዕንቁራሪት ያንቋርርብኛል! ምናለ ባይጃጃል! ምናለ የርሱንም የኔንም የሌሎቹንም ጊዜ በከንቱ ባይገድል…» በሚል እየተብሰከሰከ ነው – በዚህም አልበቃውም «ምን እንደጐማሬ ያናፋብኛል ጃል፤ ንፋስ እንደሚያርገበግበውስ ቆርቆሮ እየተንኳኳ በጆሮየ ታንቡር ለምን ይጫወታል» ይላል በውስጡ። በውስጡ ብቻ መሆኑ ግን በጀው። እህ? የእንጀራ ገመዱ እኮ ነው።

ሰንደሉ ጨሶ ጨሶ ሊጠፋ ምንም ያህል ጊዜ አልቀረውም ። መላ ቅጡ በጠፋ የሙዚቃ ቱማታ ለሁለት ሰዓታት ያህል አንጐሉ የተበጠበጠው ሴክሃር ነፍሱ ተጨንቃበት ወዶ ከገባበት አጣብቂኝ የሚወጣበትን ብልሃት እያሰላሰለ ነው። ሥልት በሌለው የሙዚቃ ኳኳታ የደነዘዘው ሴክሃር በግማሽ በድን የሆነ ያህል ተሰማው። ርዕሰ መምህሩ «ልቀጥል?» ብሎ ለመጠየቅ ባንዱ ሙዚቃውን ለአፍታ ሲያቆም ሴክሃር ተሽቀዳድሞ «ኦዎ!፣ በቃ! በቃ! እባክዎን በቃ የእስካሁኑ ይበቃወታል» ማለቱ በጀ እንጂ ርዕሰ መምህሩ በጐርናናና ለዛ የለሽ ድምጻቸው አዳራቸውንም ቢሆን ሊቀጥሉ ዝግጁ ነበሩ።

ርዕሰ መምህሩ በራሳቸው የሙዚቃ ክንዋኔ በብርቱ ተመስጠዋል። ፊታቸውም በላብ ችፍ ብሎ ዝናብ እንዳረገዘ ዳመና ተንቆርዟል። ሴክሃር ለማንም አዝኖ በማያውቅ ሁኔታ አዘነላቸው ፤ ድካማቸው ልቡን ነካው። ይሁንና ያ ሁሉ ልፋታቸው ዋጋ ቢስና ከሙዚቀኛነት ተርታ የማያሠልፋቸው መሆኑን በመገንዘቡ ምንም ዓይነት አወንታዊ ነገር እንዳይጠብቁ በኀሊናው መጸለይ ነበረበት። የሞት ፍርድ እንኳን የፈረደ ዳኛ ተሰምቶት በማያውቅ ደረጃ የመርዶው ስቃይ ገና ከመናገሩ እርሱ ራሱን አሰቃየው ። የርሱን ፍርድ ለመስጠት የርዕሰ መምህሩ ሚስት ሳትቀር ከዚያኛው ክፍል በበሩ በኩል አጮልቃ ትከታተል እንደነበረ ሲረዳ ደግሞ ለርዕሰ መምህሩ ይበልጥ ሆዱ ተንቦጫቦጨላቸው። «ሙዚቃ ዕጣ ክፍልህ አይደለችም» ብሎ እቅጩን ሲነግራቸው የሚደርስባቸውን የስሜት ስብራት በማሰብ ትካዜ ውስጥ ገባ። ታምቡረኛውና ቫዩሊንስቱ ሙዚቃው በመቆሙ ተደስተው ከጭንቀት እፎይ ብለው የሴክሃርን ፍርድ ለመስማት አቆብቁበዋል። ርዕሰ መምህሩ ዓይነ ርግባቸውን አውልቀውና ግንባራቸውን በመሃረብ ጠራርገው ሲያበቁ፤ «በል አሁን አስተያየትህን ሳትደብቅ ንገረኝ»አሉት።

«የአስተያየቴን ጭብጥ ነገልነግርዎ እችላለሁ ጌታዬ?»አላቸው ቀድሞ ባልተዘጋጀበት ድንገተኛ አኰሁዋን።

«አይ በጭራሽ! አሁኑኑ ንገረኝ፤ ግዴለህም ግልጹን ንገረኝ። ቆንጆ ነበር የሠራሁት?»

ቁርጡን ዛሬ ሳለመናገር ራሳቸው ለራሳቸው ቃል ገብተው የተከረቸሙ የሚመስሉት ከንፈሮቹ የሞት ሞታቸውን ተላቀቁና «አይ፤ የሠሩት በጥሩ ሁኔታ አይደለም ጌታዬ! ተበላሽቶብዎታል» አላቸው።

«አሃ፤ አሃ - ታዲያ በዚህ ሁኔታ በሙዚቃ መቀጠሉ ዋጋ የለውም ማለት ነው?»

«በፍጹም ባይቀጥሉበት ይሻላል ጌታዬ፤ ጽምፅዎ ለሙዚቃ የተፈጠረ አይደለም። ውሻ የሚጠራም አይመስለኝም ጌታዬ፤ቆርፍዶብዎታል።» አላቸው የራሱ ባልሆነ ሥልት አልባ ድምፅ። በበኩሉ «እውነት ተናግሮ እመሸበት ማደር» ምንም ዓይነት መስዋዕትነት ቢያስከፍል አንዴውኑ ወዶ ገብቶበታልና የአንደበቱ መርበትበት በጭራሽ

አላሳሰበውም፡፡ ይልቁኑስ ዕለቱን የእውነት መታሰቢያ አድርጐ ሳይዋሽ መዋሉ ከምን ጊዜውም በበለጠ በጣም አስደስቶታል፡፡

ሰውየውን ሊያስደስት የሚችል የተሻለ ነገር ቢያገኝ ደስ ባለው፡፡ ግን ትርፉ ድካም ሆነበት፡፡ እውነት በእውነትነትዋ እንዳለች መቀበልንና መስዋዕትነትን መክፈል፣ ግንባሩንም ሳያጥፍ መጋፈጥን መረጠ፡፡ እውነት – አለ ሴክሃር– በጠንካራ መሠረት ላይ ያረፈ ሰጥቶ የመቀበል ፍትሃዊ መደላደልን ትሻለች፡፡ እውነትን መናገር ከባድ ነው፡፡ አንዴ ከተናገሩ በኋላ ግን ሸክሙ ይቀላል፡፡ ዘላቂ እርካታም ያጐናጽፋል፡፡

ከርዕሰ መምህሩ ያማረ ግቢ ወጥቶ እቤቱ እስኪደርስ ድረስ አዕምሮው በጭንቀትና በሃሳብ ውጣ ውረድ ተወጥሮ ሰላም ሊሰጠው አልቻለም፡፡ ዛሬ ስለእውነት ብሎ እውነትን በገሃድ መስክሮ ያስቀየመው ሰው ተራ ሰው አይደለም፡፡ የእንጀራ ገመዱን ባሰኘው ቅጽበት በጥሶ ራሱንና ቤተሰቡን ለርሀብ አለንጋ ሊዳርግ የሚችል በመምህርነት የሚሠራበት ትምህርት ቤት ከፍተኛው ባለሥልጣን ነው፡፡ እናም የተለያዩ ጭንቀት ወለድ መላ ምቶች በአዕምሮው እንደጉንዳን እየተርመሰመሱ የኀሊና ዕረፍት ነሱት፡፡ የወደፊት ሕይወቱ እንደስካሁኑ በሰላማዊ ሁኔታ ሊቀጥል እንደማይችል ገባው፡፡ በትምህርት ቤቱ አሠራር የደመወዝ ዕድገትና ጭማሪ፣ የደረጃ ዕድገትና የመሳሰሉት ሁሉ በርዕሰ መምህሩ ሥልጣን ሥር ናቸው፡፡ ነገሩ በእርግጥም ያስጨንቃል፡፡ የጭንቀት አቁማዳ ተፈትቶ በሴክሃር አዕምሮ ውስጥ ሁሉም ጭንቀት ታጐረና አንዱን ሲሸኘው ሌላው እየተተካ ሊያሳብደው ደረሰ፡፡ እንደመጽናኛ ብሎም እውነትን በመሻት ስለ እውነት ሲሉ አንገታቸውን ለሠይፍ፣ደረታቸውን ለጦር፣ ምቹና ፈልሳሳ ኑሮኣቸውን ለመከራና ለሥቃይ የዳረጉ የታዋቂ ባለታሪኮችን ስምና ዝና እያነሳና እየጣለ ጊዜያዊ እፎይታን ለማግኘት ጣረ፡፡ የነሱን መስዋዕትነት ከእርሱው ጋር ሲያወዳድር ለንጽጽር እንኳን የማይበቃ ኢምንት የሆነ ያህል ታሰበው፡፡ በዚያም በብዙው ተጽናና፡፡

ዛሬ የሴክሃር ቀን አልነበረም፤ በቀኙ አልተነሳም ማለት ይቻላል – ፈቅዶ በገባበትና ለእውነት ዋቢና ጠበቃ ሆኖ የመዋል ቃል ኪዳን መሠረት፡፡ ገና ከማለዳው ያቀረበችለትን ቁርስ በማበሻቀጡ ውድ ባለቤቱን አስኮርፎ ከቤቱ ወጣ፡፡ ያ ኩርፊያም በአንድ ጀምበር በንኖ እንደማይጠፋና አሁንም ማታ ሲመለስ ተንቆርዝዛ እንደምትጠብቀው ገብቶታል፡፡ ቀጥሎ ጉዋደኞቹን አስቀየማቸው፡፡ በሦስተኛ ደረጃ የሥራ አለቃውን ሲያቀብጠው እውነትን ተናግሮ አንጀቱን እስከወዲያኛው በጣጥሶ ጣለው፡፡ በአንድ ጀምበር ከሦስት ሰዎች በላይ ሲያቀብጠው ነካክቶ አስቀየመ ፡፡ በዚህ ዓይነት – አለ ሴክሃር – በዚህ ዓይነት አካሄድ የዛሬውን ውሎዬን ለአንድ ሳምንት ብቀጥል አንድም ጓደኛ አይኖረኝም - ብወድቅ እንኳን ተነሳ የሚለኝና ትን ቢለኝ ውሃ የሚያቀብለኝ ፡፡ እውነትም እውነት ጉደኛ ናት፡፡

በቀጣዩ ቀን ርዕሰ መምህሩ ቢሮ ዘንድ ተጠራ፡፡ «ምን ሊሉኝ ይሆን?» በሚል የተደበላለቀ ስሜት ወደተፈለገበት ቢሮ አመራ፡፡ «ዕድሜ ለአንተ በነገርከኝ ጠቃሚ ምክር ተመርቼ ከአሁን ወዲያ ሙዚቃን እርግፍ አድግጌ ለመተው ወሰንኩ፡፡ ለአስተማሪው የነበረብኝን ክፍያ ሁሉ አጠናቅቄ አሰናበትኩት፡፡ እስከአሁን እንዳንተ እውነትን ሳይፈራ በግልጽ የነገረኝ ማንም የለም ፡፡ በዚህ ዕድሜዬ በማይሆነኝ ነገር ላይ ገትጋታ ሆኜ መቆየቴም ስህተት ነበር፡፡ በነገራችን ላይ የነዚያን ተማሪዎች የፈተና ወረቀት ዕርማት ጉዳይ እምን አደረስከው? » አሉት፡፡

«ጌታዬ ለነሱማ ትናንት አሥር ቀን ሰጥተውኝ የለም እንዴ ?»

«አሃ! ልክ ነህ ፡፡ ግን ሃሳቤን ለመለወጥ ተገድጃለሁ ፡፡ እስከ ነገ ጧት ዕርማቱን ጨርሰህ እንድታመጣልኝ ይሁን፡፡»

«አንድ መቶ ወረቀት በአንድ ሌሊት ታርሞ ሊያልቅ? ኧረ አይሆንም ጌታዬ! ያ ማለት 'ኮ አንድም እንቅልፍ ባይኔ ሳይዞር የነገዋ ጀምበር ቁር ትላለች ማለት ነው፡፡ ባይሆን ሁለት ተጨማሪ ቀናት ይስጡኝ ጌታዬ?!»

«በጭራሽ አላደርገውም፡፡ ይልቁንስ ሁሉም በጥንቃቄና በሚገባ ታርመው ነገ ጧት ቢሮዬ ይምጡልኝ ፡፡ ትርፍ ንግግር አያስፈልግም ወዳጄ ፡፡ በኔ በኩል ጨረስኩ!»

«እሺ ጌታዬ! ካዘዙኝ ምን አደርጋለሁ» አለ ሴክሃር፡፡ የውስጡ ስሜት ግን ሌላ ነበር ፤ «እውነትን በመናገሬ በዚህ ብቻ የምታለፍ ከሆነ ዕዳው ገብስ ነው፡፡ የእውነት መዘዝ እስከ ኅልፈት ሊዳርግ ስለሚችል ይህኛው ቅጣት፣ ቅጣት ሳይሆን ቅንጦት ነው ፡፡ የባሰ ስላለ አላማርርም – ይብስ አታምጣ ነው! »

*በገጽ 76 ለተሰጡት ጥያቄዎች መልስ*

| | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **ለእንግሊዝኛው ፡** | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 | 11 | 12 |
| **የአማርኛው ፡** | 4 | 12 | 7 | 11 | 10 | 9 | 8 | 6 | 3 | 2 | 1 | 5 |

the teacher

Contact Address


St. Mary's University College (SMUC)

**Faculty of Teacher Education**

Tel. (+251-11) 553 80 01, 553 80 21

P.O.Box 18490

Website:http/www.smuc.edu.et


# The Teacher


A Bi-annual Bulletin of the Faculty of Teacher Education, St. Mary's University College

በቅድስት ማርያም ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ የመም/ትም/ፋካልቲ በዓመት ሁለት ጊዜ የሚታተም መጽሔት

Vol. 4 No. 8 April 2011

ቅጽ. 4 ቁ. 8 ሚያዝያ 2003


## INSIDE THIS ISSUE

## በውስጥ ገጾች


| | | |
|---|---|---|
| EDITORIAL | ------ | 1 |
| RESEARCH | ------ | 2 |
| TEACHING TIPS | ------ | 24 |
| REFLECTION | ------ | 27 |
| LET'S MIND OUR LANGUAGE | --- | 50 |
| COMMENTARY | ------ | 56 |
| ቅኝት | ------ | 64 |
| ዳሰሳ | ------ | 69 |
| EDUTAINMENT | ------ | 72 |
| ልቦለድ | ---- | 77 |


## QUOTE OF THIS ISSUE

**"If one is too lazy to think, too vain to do a thing badly, too cowardly to admit it, s/he will never attain wisdom."**

**Cyril Connolly** (1903 - 1974)